መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን



Kidst Slassie Ethiopian Orthodox Tewahido Church



የመልእክት ሳጥን ቁጥር፡ P.O. Box 42204 Arlington, VA 22204 (703) 606-1976

## ሳምንታዊ አገልግሎቶቻችን

1. ዘወትር ማክሰኞ፣ ከ6-8p.m. የልጆች ትምህርት፣ ጸሎተ ሰርክ፣ ምህላ፣ ትምህርት…በ5901 Leesburg pike, Falls Church, VA 22041 (በትልቁ ቤተ ክርስቲያን)
2. ዘወትር ቅዳሜ፣ ከ6-10 a.m. ቅዳሴ፣ ትምህርተ ወንጌል፣ መዝሙር….በ5150 Leesburg pike Alexandria, Virginia 22302 (በትንሿ ቤተ ክርስቲያን)
3. ዘወትር እሁድ፣ ከ6፡00-10:00 a.m. ቅዳሴ፣ ትምህርተ ወንጌል፣ መዝሙር…(በ5901 Leesburg pike, Falls Church, VA 22041 (በትልቁ ቤተ ክርስቲያን)
4. የቴሌቪዥን መርሃ ግብር፣ ረቡዕ 8-9 p.m.፣ ቅዳሜ ከ3-4p.m.፣ እሁድ ከ5-6p.m. በቻናል 30…እንደየ ኬብል ካምፓኒው ሊለያይ ይችላል።

# የኃጢአትን ይቅርታ ለማግኘት የሚቀርብ ጸሎት

## የዳዊት መዝሙር 51

1 አቤቱ፥ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፤ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ።
2 ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥ ከኃጢአቴም አንጻኝ፤
3 እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፥ ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና።
4 አንተን ብቻ በደልሁ፥ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ፥ በነገርህም ትጸድቅ ዘንድ በፍርድህም ንጹሕ ትሆን ዘንድ።
5 እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።
6 እነሆ፥ እውነትን ወደድህ፤ የማይታይ ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ።
7 በሂሶጵ እርጨኝ፥ እነጻማለሁ፤ እጠበኝ፥ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ።
8 ሐሤትንና ደስታን አሰማኝ፥ የሰበርሃቸውም አጥንቶቼ ደስ ይላቸዋል።
9 ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ፥ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ።
10 አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።
11 ከፊትህ አትጣለኝ፥ ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ።
12 የማዳንህን ደስታ ስጠኝ፥ በእሽታ መንፈስም ደግፈኝ።
13 ለሕግ ተላላፎች መንገድህን አስተምራለሁ፥ ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ።
14 የመድኃኒቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ ከደም አድነኝ፥ አንደበቴም በአንተ ጽድቅ ትደሰታለች።
15 አቤቱ፥ ከንፈሮቼን ክፈት፥ አፌም ምስጋናህን ያወራል።
16 መሥዋዕትን ብትወድድስ በሰጠሁህ ነበር፤ የሚቃጠለውም መሥዋዕት ደስ አያሰኝህም።
17 የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፥ የተሰበርውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም።...

“የሰዎችን በደል ይቅር ብትሉላቸው እናንተንም የሰማዩ አባታችሁ ይቅር ይላችኋል።”
ማቴ 6፡14

“የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ባትሉላቸው ግን የእናንተንም በደል የሰማዩ አባታችሁ ይቅር አይልላችሁም።”
ማቴ 6፡15

አዘጋጅ ሊ/ኅ ቀሲስ ይስሐቅ ወልደ ማርያም

ጥያቄ ካላችሁ በ(703) 606-1976 ደውላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ።